# አዲስ አበባ የዘረኛች ሳትሆን የሸዋ ክ/ሐገር ዋና ከተማ ናት!!

February 23, 2016

(ከተስፋዬ መኮንን)

በቅድሚያ የሽግግር ጊዜ ውስጥ መግባታችንን አስመልክቼ በወልቃይት ድሕረ ገጽ ላይ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ቀደም ብሎ ባቀረብኩት መጣጥፍ ገልጬ ነበር። ለአንባቢዬ ግልጥ ይሆን ዘንድ ይህ የጀመርነው የሽግግር ጊዜ ከወያኔ ሞት በኋላ የስልጣን መደላድልን ስምረት ለመስጠት ከሚመጣ የአጭር ጊዜ የሽግግር ወቅት ጋር እንደማይመሳሰል ላሳስብ እወዳለሁ። በትግል የተግባር ይዘት ይለያያሉ። አንዱ ለድል ለመብቃት የሚደረግ የግብግብ ወቅትን ሲያመለክት ሁለተኛው ባለድላማውን ትግል መሰረት ለማሲያዝ የሚያስፈልግ የመሰናዶ ጊዜን ያመለክታል።

የዚህን ተጀመረ የምለውን የግብግብ የሽግግር ጊዜን እውን መሆን የሚያበስሩ ብዙ የትግል ትእይንቶች እየተከሄዱ መሆናቸውን አይነ-ህሊናውን ከፊት ለማድረግ ለቻለ ገሀድ ነው። የትግል አሰላለፎች ጥራታቸውን እየያዙ ነው። ግለሰቦች ሳይቀሩ ባደባባይ ከወደትኛው የትግል ጎራ እንደቆሙ እያወጁ ነው። የብዙሀን መገናኛዎች ሽፍንፍናቸውን ጥለው ሚናቸውን ለይተዋል። የወያኔ አልጋ ወራሾች እነማን እንደሆኑ ያደባባይ ሚስጢር ሆኗል። ምሁሩ በግልጥ ለሁለት ተከፍሏል። ከዚህ ሰልፍ ውጪ የቆመውም አድርባይ የሚደበቅበት ጎራ ጠፍቶት እርቃኑን ቀርቷል።

የዚህ የግብግብ የሽግግር ጊዜ እውነተኛ ማሰሪያ ጥብጣቡ በሰሞኑ ተላከ ካቶ ሌንጮ ለታ ደረሰ ለወያኔ የሆነው የስላጣን አስረክቡን ደብዳቤ መሆኑን አይተነዋል። ይህ ደብዳቤ ግድግዳው ላይ የተጻፈውን የማይታጠፍ መልእክት በወግ የማንበብን አስፈላጊነትን አበክሮ በማስጠንቀቅ መልእክቱን ያስተላልፋል። ቀጥሎም ሁለት መሰረታዊ የሆኑ የኦነግን ጥያቄዎች በወያኔ እንዲመለሱ ያቀርባል። እነሱም፡-

1. አዲስ አበባ ወደ ኦሮምያ ብሄራዊ መንግስት እንድትመለስ በማያሻማ መንገድ እንዲታወጅ （አቶ ሌንጮ ባረቀቁት ህገ-መንግስት ለከተማዋ የተሰጣትን የራስ ገዝ አቋሟን ገፈው በመጣል ማለት ነው።） የአዲስ አበባን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን ዴሞክራሲያዊ መብት የገፈፈና እንደ ባሪያ በመቁጠር የተሰነዘረ ስድብ። ከኦነግ ምን ይጠበቃል።

2. በአስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ የኦሮምን ጥያቄ እልባት የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲፈጠር የሚል ነው። በዘወርዋራ አካሄድ የዘር ህገ መንግስቱ ባለቤት እኔነኝ እናም አልጋ ወራሽነቱ የኔ ነው። ስለርክክቡ እንነጋገር ነው። ይህ ካልሆነ ጊዜው ይመሽና የማይቀረውን እውነታ ባሳዛኝ መልኩ እንዲስተናገድ ታደርጉታላችሁ የሚል ነው። በደብዳቤው የዋና ከተማዋ የባለቤትነት ጥያቄም የቀደመው ለዚህ መሆኑም የሚታይ ነው። ይህ ከላይ የምናየው ጥያቄ ኢትዮጵያን ለመበተን የተነሱት አክራሪዎች ደርሰንበታል የሚሉትን እድገታቸውን የሚያሳየው አስፈሪው የሽግግር ወቅቱ ስዕል ነው።

በኛ ለአንድነትና ለፍትህ ከቆምነው ኢትዮጵያውያን ዘንድስ ያለው ስዕል ምን ይመስላል? ገና ብዙ መሰራት የሚገባቸው የተበታተኑ የሽግግር ተግባሮች ይጠብቁናል። በጊዜ መቀደማችን እንዳለ ሆኖ ማለት ነው። በጣም የበዛ የአንድነት ሀይል ተስፋ ቆርጦ ተቀምጧል። ይህን ሀይል ማስነሳት ይኖርብናል። የበዛ የአንድነት ሀይል በተለያዩ ድርጂቶች ስር ተግባር አልባ ሁኖና ቁጭ ብሎ እርስ በርስ ይተያያል። ይህ ሀይል የድርጂት ድንበርን እየሰበረ መገናኘትና መቀላቀል አለበት። የበዛው ወገን ግራ ተጋብቶ መሀል ላይ የቆመም አለ። ሌላውም የትግል “እውቀቱም ተሞክሮም የለኝም” በሚል እራስን ዝቅ በማድረግ ለናት ሀገሩ ሊያበረክት የሚችለውን ነፍጓት ይገኛል። ሌላው በወያኔና በኦነግ ያላሰለሰ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ በመሆን የአንድነት ሀይልን ከአምባገነንነት ጋር የማያያዝና ያጠለቁለትን የጾረ ብሄረሰብ እንጥልጥሎሹን ያልጣለው ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ የበዛ ነው። ይህን በተለያየ ሽፍንፍን ተበትኖ የሚገኘን ህዝብ በአንድ ትልቅ የትግል አሸንዳ ውስጥ ከተን ወደማይበገር ሀይል ለመለወጥ ካልቻልን ያለጥርጥር አክራሪዎች ዛሬም እንደ ትናንቱ በውጪ ሀይል ተደግፈው ሀገራችንን ይበትኗታል። የውጪው ሀይልም

ከኋላቸው ቁሞ በገንዘብና በፕሮፓጋንዳ ዛሬም እንደትናንቱ በቅንብር እየሰራ ነው። ይህ የኛው ስእል የሚያሳየው እንደ ሁሌውም በጣም ወደኋላ መቅረታችንን ነው። አደጋውም ይህ ነው።

ከዚህ በመምጣት ላይ ካለ አደጋ እንዴት ነው የምንድነው? በእኔ እምነት መዳኛው አንድ መንገድ ብቻ ነው። ይህም የፖለቲካ ድርጂት፣ ንቅናቄ፣ ስቪል ማህበራት፣ የወጣት፣ የሴት ማህበራትና የሰባዊ መብት ተሟጋቾችና የሙያ ማህበራት በአንድ ላይ መጥተው አንድ ሐገር አድን ግንባር የመመስረቻው ጊዜ ዛሬ ነው። የዚህ ሀገር አድን ግንባር መመሪያ ምን ይሆናል? መመሪያው ኢትዮጵያን ማዳን ነው። ሲዘረዘር ግለሰቡ የፖለቲካ እምነቱን ሳይጥል፣ ፓርቲውና በፖለቲካ የተደራጀው ፕሮግራሙን ሳያጥፍና ፀጉር ስንጠቃ ውስጥ ሳይገባ ዓላማውን ይበልጥ የሚያስፋፋበት መድረኩ መሆኑንን ተገንዝቦ፣ በሙያ፣ በጾታና በውጣት የተደራጀው ለነገ ነጾነትና የሀገር ባለቤትነት መስራት
መሆኑን አውቆ እርስ በርስ መያያዝ የግድ ይላል።

የሀገር አድኑ ግንባር የሚቆምባቸው ሁሉንም አስማሚ የሆኑ ምሶሶዎቹ እነየቱ ናቸው?

1. በግለሰብ ሰብአዊ ፍጡሩ የተሟላ ነጻነት ለይ ያጠነጠነ፣ በዚህ ነጻ ሰው ውሳኔ ከታች እስከላይ ለሚገነባ ፈደራላዊ ስርአት እውን መሆን አብሮ መቆም።

2. የታጠፈው፡ የመሬት ላራሹ እንደገና በተግባር ላይ ይውል ዘንድ አንዳንድ የጋራ ሀገራዊ ፋይዳ ካላቸው መሬቶች ውጪ ያለውና ዛሬ በአዲሶቹ የጎጥ ባላባቶች ተጠቅልሎ የተያዘው መሬት ተመልሶ በአራሹ ገበሬ የግል ይዞታ ስር እንዲማጣ መታገል።

3. ዘረኝነትን፣ ጥላቻን፣ በቀልንና የበላይነት መስበክን አላማው ባላደረገ ተልእኮ ስር የቆመ ማንኛው ዜጋ የመደራጀት መብት እንዳለው ማወቅና ለተግባራዊነቱ መታገል። ሀሳብን በማንኛውም መንገድ መግለጥ የሰብአዊ ፍጡር ልዩ መለያው መሆኑን ማወቅ።

4. ስልጣን ከህዝብ ይመነጫል። መልሶም እሱን ያገለግላል። በሱም ይሻራል የሚለውን የማይለወጥ መመሪያን መቀበል።

5. ህዝቡ ይህን በጠባቦች የተነጠቀውን ስልጣኑን ለማስመለስ በሚያልፍበት የትግል ጎዳናው ውስጥ እንደሚነሱት የትግል አይነቶች ስልቱን እየቀየየረ መታገል እንዳለበት መቀበል።

በዚህ ሀገር አድን ግንባር ዙሪያ የተሰባሰቡ ወገኖችን በወቅቱ የትግል ጥያቄ ዙሪያ የተቀናጀ ትግል እንዲያደርጉ የሚመራቸው ማእከላዊ እዝ የመኖር አስፈላጊነት አየጠያይቅም ከዚህ ማእከላዊ እዝ የሚወጣውን የትግል መመሪያ ሁሉም ባለው የራሱ የድርጂት አሰራር አላማውን ተግባራዊ ያደርጋል። ሁሉም ባለው የድርጂት አቅምና ተሞክሮ ላይ ተመስርቶ የጋራ መመሪያውን ተግባራዊ ያደርጋል። እነዚህ ከላይ የተቀመጡት ምሶሶዎች በጽኑ የህዝብ መሰረት ላይ ሳይዋቀሩ የማንም የፖለቲካ ግለሰብ ምኞትም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲ የስልጣን ዓላማ ተግባራዊ አይሆንም። ለሁሉም ይህንን እውነት መገንዘብ የሚያዋጣ ይሆናል። ይህንን መሰረታዊ እውነት ስንገነዘብ ለስኬታማነቱ ለመረባረብ ረድፍ እንይዛለን።

ይህን ግንዛቤ ያገኘ ወገን ከአቋሙም ሆነ ከእምነቱ እንዲጥል የሚጠየቀው ነገር የለም።

የሚጠየቀው የነገ ቤትህን በጋራ ከጥፋት ለማዳን ተቀናጅተህ ተነስ ነው።

እንደ አብነት አንድ ሁለት ብለን የትግል ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ ባቶ ሌንጮ ለታ የተሰነዘረውን የአዲስ አበባን የይገባናል ጥያቄን እኛ የተባበርን የአንድነት ሀይሎች እንዴት እንመለከተዋለን?  የሚለው አንዱ ነው። ጥያቄው ግለሰቡ ከሚመሩት ግንባር ኢትዮጵያን የመበተን ዓላማ አንጻር የሚጠበቅ መሰረታዊ ጥያቄ ነው። ቀዳሚ ጥያቄያቸው ሆኖ

መቅረቡም አይደንቅም። ለኛም ጥያቄው የኢትዮጵያን መሀል መትቶ የሚበትናት በመሆኑ የህልውናችን ዋና ጥያቄ ያደርገዋል። ይህን የዘረኞችን አከርካሪያችንን የመምታት ሴራን የማክሸፍ ተግባር የመላው የአንድነት ሀይሎች ተግባር መሆኑ ለአንዴም መረሳት የለበትም። ይበልጥ ደግሞ እኛ የአንድነት ሁይሉ አባል

የሆንን የከ/ሀገሩ ተወላጆች በግንባር ቁመን የምንዋደቅለት የትግል ድርሻችን ይሆናል።

ከሁለት ወራት ቀደም ብዬ በወልቃይት ድህረ ገጽ ላይ "ሸዋማ ሸዋ ነው ሀገር ኢትዮጵያ" ነው በሚል የሸዋን ልዩ ታሪክና የህዝቦቿን ቅልቅልና ማንነት ገልጫለሁ። በመሆኑም የራሱን ከ/ ሀገራዊ ፌደራላዊ መስተዳደርን እውን የማድረግ ሙብቱን አመልክቻለሁ። የአዲስ አበባም ህዝብ የዚሁ ቅልቅል ህዝብ አካልና ወለላው መሆኑን አስታውሻለሁ። ከተመዋም በታላቋ የታሪክ ሰው በጣዬቱ ብጡል በ1979 ዓም እስከተመሰረተችበት ጊዜ ድረስ መሬቱ ከአራቱም የሀገሪቱ ማእዘናት በጎረፉ ህዝቦች የተማከለ የነበር ነው። ከዚያም በኋላ ይህ መከተምና መቀላቀል እንደቀጠለ ነው። ወደፊትም ማንም እኔነኝ ባይ ሳያቆመው የሚቀጥል ይሆናል። ከእንግዲህ በማንም አንድ የቋንቋ ተናጋሪ የበላይነት ሙብቱና ነጻነቱ ተረግጦ አይቀጥልም።

እንግዲህ አምባገነኑ ጎጠኛ ይህ መሬት የብቻዬ ስለሆነ ወይ በኔ ስር ተገዙ ካልሆነም ልቀቁ ሊለን ነው። ዛሬ የሸዋ ልጅ በየፈርጁ ተደራጅቶ መታገል ያለበት ይህን የጠባቦችን ሴራ ነው። የሸዋ ብሎም የኢትዮጵያ ልጅ የተፋውን የአቶ ሌንጮን የዘውግ ስርአት መልሶ አይልስም። እሱ የውሻ ባህሪ ነው። እናም የከ/ ሀገሩ ህዝብ በሚሰጠው ህዝበ ውሳኔ ህልውናውን በጁ እንደሚያደርግ አንጠራጠርም። እኛም የምንታገለው ዋና ከተማውን ጨምሮ መላው የከ/ ሀገሩ ህዝብ ስለወደፊቱ የአስተዳደር ምኞቱ ነጻና ዲሞ ክራሳዊ በሆነ መንገድ ህዝበ ውሳኔን እንዲያደርግ ነው። ይህ ሙብቱ ነው።

ሌላው እንደ ምሳሌ ልንጠቅሰው የሚገባ ቋንቋንና ማንነትን አብሮ በማሰር ዘረኞች የሚነዱትን ፖለቲካ እንዴት ማክሸፍ ይቻላል? የሚለውን መመልከት ይቻላል። ለኛ ለአንድነት ሀይሎች በሀገራችን የህዝብ መገናኛ ሆነው የሚያገለግሉት ቋንቋዎች በሙሉ የህዝቡ ሀብቶቹ ናቸው። በመርሀና በመንፈስ የትኛውም ቋንቋ ከሌላው አይበልጥም። ይነስም ይብዛ የሰውን ልጆች በማገናኘት አግልግሎት ይሰጣሉና እናከብራቸዋለን። በራሱ በህዝቡ የታሪክ ጉዞ ዳብረውና ጎልምሰው የተለያዩ ቋንቋዎችን ድንበር በመሻገር የሁሉም የጋራ መግናኛ የሆኑትንም ቋንቋዎች የህዝቦች የአንድነት መገለጫቸው አድርገን እንወስዳቸዋለን። ቋንቋ ከዚህ ውጪ ምንም የፖለቲካ እንጥልጥሎሽ ሊወጣለት አይችልም።

ለህዝባችን የመገናኛ ተግባር በቀላሉ እንዲያገለግለው፣ ቋንቋው እንዳይረሳ፣ እንዳይጠፋና ለልጆቹ በቅርስ እንዲተላለፍ በሀገሪቱ የትምህርት ስርአት ውስጥ እንዲካተት መስራት የሚቀድም ስራችን ይሆናል። ከነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ የበዙ ህዝቦችን የሚያገናኙ ቋንቋዎችን የሁሉም ህዝብ መገናኛ ቋንቋ ይሆኑ ዘንድ በህግ ድንጋጌ ማእቀፍ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ የምንታገልለት ይሆናል። ለቋንቋ እድገት ወሳኙ ከምልአተ ህዝቡ እንዳይለይ ማድረግ ነው። ለምሳሌ የኦሮሞ ጠባቦች የፖለቲካ መጫወቻቸው ያደረጉትን የማህበረሰቡን ቋንቋ የማያስፈልግ ፊደል በመስጠት ከኢትዮጵያ ሰፊ የእውቀት መአድ ነጥለው በአንድ አካባቢ ወስነውታል። ለመነጠል ፖለቲካቸው ለአጭር ጊዜ ሊያገለግል ይችል ይሆናል። በቋንቋው ላይ ግን የሞት ፍርድ ነው የፈረዱበት። ቋንቋው የሚያድገው በኦነግ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ አይደለም። ቋንቋው የሚያድገው የሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት መሆኑ ታውቆ ሁሉም እንዲማረው፣ እንዲሰራበት፣ እንዲመራመርበት፣ እንዲናገድበት፣ በፍትህ አደባባይ እንዲዳኝበትና ልጆቹም በአመራር ችሎታቸው መልሰው ሀገራቸውን የሚያገለግሉበት ቋንቋ መሆኑን ስንገነዘብ ነው። የኦሮሞም ሆነ የሌላው ቋንቋ ተናጋሪ ሰው ማንነቱ ከማንኛውም ጭቆና ነጻ መውጣቱ ነው። ቋንቋውን በሚናጋር ተረገጠ ወይም በሌላ የተሰጠው ማንነት ባርነት ነው። ሰው ከዚህ ባርነት ነጻ ወጣ ማለት አንጻራዊ ማንነቱን አስመለሰ ማለት ይሆናል።

እኛ ከአርባ አንድ ዓመታት ቀደም ብሎ "መሬት ላራሹ" ብለን በግንባር ከቆምነው ውስጥ የበዛነው ከፊውዳሉ መደብ ዘንድ፣ ከባለብዙ፡ ጋሻ ባለመሬት ከሆኑ ቤተሰብ ዘንድ የመጣን ነበርን። ከወላጆቻችን ከነወዳኛው የተለያየነው በዚህ የፖለቲካ

አቋማችን ነበር። እንዲህ ሁነን የታገልንለት ጥያቄ ዛሬ በጠባብ ዘመናዊ ባላባቶች ታጥፎ መሬቱን በጃቸው አስገብተውታል። ይሸጡታል፣ ይለውጡታል። ለባእድ ሀገርም አሳልፈው ወሮታ መክፈያ አድርገውታል። ከፊውዳል ጪሰኝነት ነጻ እንዲወጣ የታገልንለት ጭሰኛም መልሰው የነሱ ገባር አድረገውታል። እናም ጥያቄው እንደገና የምንታገልለት ሆኗል። በዚህ አንጻር ከግልና ከፓርቲ አመለካከት ባሻገር ለአንድነት ሀይሎች የመታገያ የጋራ ጥያቄዎቻችን የበዙ የፓርቲ ናቸው። በመሆኑም የነቃው ወገን አናሳ የድርጂትና ጠባብ የፖለቲካ አመለካከቶች ሳያግዱን ለጋራ ሀገራዊ ጥያቄዎች እውን መሆን ጊዜ ሳይቀድመን ልንረባረብ ይገባል።

በዚሁ አኳይ ለሁሉም የአንድነት ሀይሎችና በተለይም ከሀገሪቱ አራት ማእዘን ተሰባስባችሁ ሸዋ ክ/ ሀገርን የመኖሪያ ቤታችሁና መቀበሪያችሁ ያደረጋችሁ ህዝቦች ይህ ክ/ሀገር የናንተ ሀገር ነው። ይህንን አውቃችሁ ዘረኞች በመሀከላችሁ የተከሉትን የጎሳ ችካል በመንቀል እጅ ለእጅ ተያያዙ።ሳትከፋፈሉ የክ/ሀገራችሁን የወደፊት እጣ ፈንታ የምትወስኑት እናንተ ብቻ መሆናችሁን አውቃችሁ በአንድነት ለከፋፋዮች ሴራ እምብኝ በሉ። የአዲስ አበባም ህዝብ የዚህ ክ/ ሀገር ዋና ከተማ፣ የነገ ፈደራላዊትና ፍትሃዊት ሀገራችሁና የአፍሪካ መዲና ባለቤት መሆኑን ተገንዝቦ ትግሉን ማፋፋም ይገባዋል። ዘረኝነትንና ጎጣዊ አገዛዝን የምንቀብረው በእኒህ ከሁሉም ህዝቦቿ ዘንድ በተሰባሰቡና በአንድነት በሚቆሙ ኢትዮጵያውያን እንደሚሆን አንጠራጠርም። ለዚህ ድል ለመብቃት ወሳኙ ሁሉም በየፈርጁ መንቀሳቀስና መደራጀቱ ነው። ይህን የተቀደሰ ዓላማ በክ/ ሀገሩ ህዝብ ውስጥ ማሰራጨቱ ወሳኝ ይሆናል። ሃሳብ ተሰራጭቶ የሁሉም ሲሆን ወደ ማይበገር ቁሳዊ ሀይል ይሸጋገራል። ለዚያ እውን መሆን የቀደመንን ጊዜ እንቅደመው።

**ኢትዮጵያ ከአንድነት ሀይሎች ጋር ለዘለዓለም ትኑር!!**